በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የተሰጠ መግለጫ

ግንቦት 8 , 2005 ዓ.ም

**የውድቀት አደጋ ያንዣበበባቸው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆችና ተቋማት**

በአሁኑ ወቅት የወያኔ መንግሥት ለመዘርጋት አመቻቻለሁ ብሎ ለሚነግረው መሠረተ ልማት ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ሥራ እንዲሁም በኮንስትረክሽን ፍላጎት አንፃር በርካታ ሙያተኞች ለነዚህ የሥራ መስኮች ያስፈልጋሉ። እነዚህ ሙያተኞች ሰልጥነው ከሚወጡባቸው የትምህርት ተቋማት አንዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ኮሌጅ ነው። ሆኖም ከኮሌጆቹ ብዙ ቢጠበቅባቸውም ከችግር ውስጥ ከመዘፈቅ አልወጡም። ተቋማቱ የጠራ አስተዳደራዊ መዋቅር የሌላቸው ፣ የአመራርና የአፈጻጸም ብቃት የጎደላቸው ፣ የሰው ኃይል አጠቃቀም ፣ የፋይናንስ ሥርዓት ፣ የትምህርት መሣሪያዎች ግብአት ፣ የተማሪዎች ምደባና ሌሎችም ግድፈቶች የሚታዩባቸው ሆነዋል።

ኮሌጆቹና ተቋማቱ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ያልተሰራባቸው በ10ኛ ክፍል መልቀቂያ ሀገር አቀፍ ፈተና ዝቅተኛ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች ለስልጠና የሚመደቡባቸው በቂ እውቀትና ክህሎት ያላቸው መምህራን ያልተሰማሩባቸው የትምህርትና የስልጠና ዘርፍ ናቸው።

በመምህራን ላይ የሚታየውን የእውቀትና የክህሎት ክፍተት ለመሙላት አጫጭር ስልጠናዎችና የክረምት ኮርሶች ቢሰጡም የትምህርቱ ጥራት ዋነኛ መመዘኛ መስፈርት የፖለቲካ ታማኝነት የሚለው ስንኩል የወያኔ አስተሳሰብ ገኖ በመወጣቱ በርካታ ልምድ ያላቸው መምህራን ሥራቸውን እየለቀቁ በመሄዳቸው የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችና ተቋማቱ በአሁኑ ጊዜ ይበልጥ ተዳክመዋል። በከፊልና ሙሉ በሙሉ ወደመዘጋት በማምራት ላይም ይገኛሉ።

የቴክኒክና ሙያ ከስሙም መረዳት የሚቻለው ለአንድ ሀገር ዕድገት በጣም አስፈላጊ የትምህርት ዘርፍ በመሆኑ ከፌዴራል መንግስት እስከ ኮሌጆችና ተቋማቱ ዝቅተኛ የዘርፍ አስተባባሪ ድረስ አስተዳደራዊ ችሎታና የቴክኒክ ክህሎት ያለው አመራር እንደሚጠይቅ አያጠራጥርም። ሆኖም ግን በአሁኑ ጊዜ የአመራር ቦታው የሚያዘው አስተዳደራዊ ስነ ምግባር በጎደላቸው መሰረታዊ የአመራር መርሆዎች ትውውቅ እንኳን በሌላቸው የቢሮአቸውን ግድግዳ በፎቶግራፍና በጥቅስ ከማሸብረቅ ባለፈ አዳዲስ የአሰራር የክትትልና የቁጥጥር ዘዴዎችን መቀየስ በማይችሉ የወገንን ዘላቂና የጋራ ጥቅም በጊዜያዊ የግል ጥቅም የሚሸጡ ሙስናን ለመጠየፍ የሞራል ግዴታና ብቃት በሌላቸው እበላ ባዮች ነው። በመሆኑም ኮሌጆቹና ተቋማቱ እውቀትና ችሎታ ባላቸው ሙያተኞች በዕቅድና በፕሮግራም መመራት ሲገባቸው የዕውቀት ድሃ በሆኑ ሆድ አደር ካድሬዎች በሚሰጡት ፖለቲካዊ ትዕዛዝ የሚመሩ በመሆናቸው ሰልጣኞች ተገቢ የሙያ ብቃትና ክህሎት ጨብጠው አይወጡም። ይህም በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ሥራ አጥተው በመንከራተት ላይ ይገኛሉ።የወጣቶች ሥራ አጥቶ መንከራተት የሙያው ማሰልጠኛ ኮሌጆችና ተቋማት አመራሮችንም ሆነ በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የመንግስት ባለሥልጣናትን የሚያስጨንቃቸው ጉዳይ አልሆነም። ይልቁንስ "የባለራዕይ" መሪ ፎቶግራፍ ግድግዳ ላይ ያለመለጠፍ ይበልጥ የሚያባትላቸውና ሌላውም የፖለቲካ ሥራ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጡት ሆኖ ነው የሚታየው።

የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችና ተቋማት የስልጠና ማእከላት እንደመሆናቸው መጠን በቋሚ ንብረትነት ያሉ ማሽኖችና ልዩ ልዩ የማምረቻ መሳሪያዎችና ለስልጠና የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች ለየስልጠና ዘርፉ እንዲደርሱ ለማድረግ ብቃትና ታማኝነት ባላቸው ሙያተኞች ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል። ሆኖም ግን በዚህ የሥራ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች ዕውቀት ፣ ብቃትና ስነ ምግባር የወረደ በመሆኑ ንብረቶቹ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከማድረግ ይልቅ ሆን ብለው



P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የሥራ መጓተትን በመፍጠር የሙስና መረቡ እንዲደነደን የሚያደርጉ ናቸው። በተለይም በየዓመቱ መደረግ የሚገባው የንብረት ቆጠራ ፈጽሞ የማይታሰብ በመሆኑ የተገዙ ዕቃዎች ንብረት ክፍል መግባቱ ቀርቶ በኮሌጆቹና በተቋማቱ ግቢ ሳይደርሱ አየር ባየር ይቸበቸባሉ። በየስልጠና ኮሌጆቹና ተቋማቱ አሉ የተባሉ ማሽኖችም ውስጣቸው ቢፈተሹ በቀዶ ሕክምና የውስጥ ብልቱን እንዳጣ ሕመምተኛ ባዶ ሁነው የሚገኙ ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

ዛሬ በየሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆችና ተቋማት የተንሰንራፋውን ሙስና ላየ ፣ የኦዲትና ቁጥጥር አገልግሎት በአግባቡ አለመከናወኑን ለተመለከተ ቋሚ ንብረቶች ጄኔሬተሮች ሳይቀሩ ለግል ነጋዴ ሲቸበቸቡ ላስተዋለ፣ በአጠቃላይ የፋይናንስ እንቅስቃሴው በዘራፊ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ካድሬዎች ተይዞ ዝርፊያው ሲጧጧፍ ለምን? ብሎ የሚጠይቅ ካለ ሞኝ ያለበለዚያ ፀረ-ልማት ፣ የልማት አደናቃፊ ኃይል ተብሎ በመፈረጅ የአጥፊዎቹ ምግባር እንዲላከከበት ይደረጋል።

በመምህራን ላይም ከሚፈጸሙ በርካታ ኢፍትሀዊ ተግባራት መካከል በቅጥር ፣ በዝውውርና በዕድገት መመሪያ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶች ወደ ጎን እየተገፉ በፖለቲካ ታማኝነታቸው ብቻ ደመወዝ የሚጨመርላቸው የገዢው ፓርቲ (የወያኔ/ኢህአዴግ) ታማኞች እንዳሉ ሁሉ አንድ ቦታ ተረስተው አስተዋሽ ያጡ ግን ለሥራ ደፋ ቀና የሚሉ ፣ ስለስራቸው የሚመሰከርላቸው አጥተው አንገታቸውን ደፍተው የሚኖሩ በርካታ ቁጥር ያላቸው ትጉሕ መምህራን በየማሰልጠኛ ኮሌጆችና ተቋማት ይገኛሉ።

በተለይም ከደረጃ ማስተካካያና ከደመወዝ ጭማሪ ጋር ለሁሉም መምህራን ደመወዝ ተጨምሯል በሚል ሰበብ አብዛኛው ነባር የሆኑ የደረጃ B መምህራን ከነበሩበት የደመወዝ ደረጃ ዝቅ እንዲሉ መደረጋቸው የአሰልጣኝ (*Instructor*) የደረጃ ማዕረጎችን ስያሜ በመሰየም ለደረጃው የተቀመጠውን የደመወዝ እርከንና ጥቅማጥቅም እንዳያገኙ ማድረግ ፣ ተጨባጭነት የሌለው ተስፋ መስጠት ፣ መዋሸት ፣ መምህሩን በድፍረት መዘለፍና ማሸማቀቅ ፣ በከተማዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ዘርፍ ለአምራች የግልና የማህበር የንግድ ተቋማት የሙያ እገዛ መስጠት በሚል ሽፋን የመምህሩን ክብር ዝቅ በሚያደርግና ጤናውን አደጋ ላይ በሚጥል መልኩ ሰጋቱራ ፣ አቧራና የመጸዳጃ ቦታዎችን እንዲያጸዱ ማድረግ በመምህራን ላይ ከሚደርሱ በደሎችና ከሚፈጸሙ ግፎች ጥቂቶቹ ናቸው።

በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የሚታየው አንዱና አሳሳቢው ችግር የስልጠና ጥራት መጓደል ነው። ምንም እንኳን የስልጠና ጥራት ከብዙ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ የሚቃኝ ቢሆንም የአሰልጣኙ ብቃት፣ የማሰልጠኛ መሳሪያዎቹ ደረጃና በበቂ ሁኔታ መገኘት ፣ የጥሬ ዕቃዎች አቅርቦት፣ የአስተዳደሩ በሳል አመራር ሰጭነት ፣ የሰልጣኙ ፍላጎትና የመቀበል ችሎታ የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛሉ። ሆኖም ግን ከላይ የተጠቀሱት ለትምህርት ጥራት መሻሻል ወሳኝ የሆኑ ግብአቶች አለመሟላት ለነባር መምህራን በከፍተኛ ደረጃ መፍለስ በዋና ምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። በመሆኑም የነባር መምህራን ፍልሰት ለመቀነስ አዳዲስ የ C ደረጃ መምህራን ቦታውን እንዲይዙት እየተደረገ በመሆኑ የስልጠናው ጥራት እየቀነሰ የሰልጣኞች ቁጥርም እየተዳከመ መጥቷል። ለዚህም ማስረጃ ሊሆን የሚችለው በ2005 ዓ.ም በቴክኒክና ሙያ ለመሰልጠን የተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር በ80% ቀንሶ መታየቱ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም በሚቀጥሉት አጭር ተከታታይ አመታት የማሻሻያ እርምጃዎች ካልተወሰዱ በስተቀር ሕንፃዎቹ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት መታሰቢያ ሀውልት ሆነው እንደሚቀሩ አያጠራጥርም።

በሌላ በኩል የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችንና ተቋማትን እየተፈታተነ የሚገኘው አሳሳቢ ችግር የሥርዓተ ትምህርቱ ተለዋዋጭ መሆኑ ሲሆን ይህም የሚሰጠው ስልጠና በሰልጣኞች ላይ ያለመታማመን ስሜት እንዲፈጠርባቸው እና ተስፋም እንዲቆርጡ እያደረጋቸው ነው። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በመጀመሪያ ስልጠናው ሲሰጥበት የነበረው የትምህርት ደረጃ 10 +1 ፣ 10+2 ( ሰርቲፍኬት)፣ 10 +3 (ዲፕሎማ) የነበረው ተወግዶ ደረጃ አንድ ፣ ደረጃ ሁለት፣ ደረጃ ሶስት ፣ ደረጃ አራትና ደረጃ አምስት በሚሉ የማስመረቂያ መንገዶች መተካቱ ነው።ለዚህ ስርአተ ትምህርቱ ሲዘጋጅ የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ፣ የሕብረተሰቡን አመለካከት ፣ የግብአት አቅርቦትን ያላገናዘባ ከመሆኑም ሌላ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች አስተያየትን ያለካተተ ነው።



P.O. Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • EMail: eta941@yahoo.com

የቴክኒክና ሙያ ስራዎች በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የሚከናወኑት በመመሪያና ደንብ ሳይሆን በየጊዜው በሚላኩ ተራ ደብዳቤዎች ተመስርቶ አንድ ለአምስት በሚለው ፖለቲካዊ አደረጃጀትና የልማት ቡድን መሆኑ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችና ተቋማት በጥናት ላይ የተደገፈ አቅጣጫ ያልተቀመላቸው ለመሆኑ ማስረጃ ነው።

ከዚህም አልፎ ተርፎ ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ( *Occupational Standards*) ይዘቶች ያካባቢውን ነባራዊ ሁኔታና የመምህራንን አቅም ያላገናዘቡ ፣ የመምህራንን አቅም ለማጎልበት ተብለው የሚሰጡ ስልጠናዎችም ከሙያው ጋር ተያያዥነት የሌላቸው ባብዛኛው በፖለቲካ ጉዳይ ላይ ያተኮሩ ናቸው።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ጥራት የጎደለው በመሆኑ በጥሩ ዋጋ ሊሸጥ የሚችል ጥሩ ገቢ የሚያገኝ ሙያተኛ ለማፍራት አልቻለም። ምሩቃኑም ቢሆኑ ገበያው የሚፈልገው ዓይነት ብቁ ሙያ የላቸውም። ብዙዎቹ በተመሳሳይ ሙያ የተመረቁ ስለሆኑ ስራ የማግኘቱን ጉዳይ የበለጠ አስቸጋሪ ያደርገዋል። ከዘመኑም ቴክኖሎጂ ጋር የሚራመድ ሙያዊ ብቃት የላቸውም። አስፈላጊውን እውቀት ከኮሌጆችና ከተቋማት ይዘው አይወጡም። የዚህ ዓይነት ባለሙያ አንድን ሀገር ከድህነት ያወጣታል ተብሎ አይታሰብም። ስለሆነም ሁሉም አገር ወዳድ የችግሩን አሳሳቢነት ተመልክቶ የውድቀት አደጋ እያንዣበበባቸው የሚገኙትን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፎችን ለመታደግ መረባረብ ያስፈልጋል። የችግሩ ምንጭም የወያኔ/ ኢሕአዴግ ሥርዓት በመሆኑ ይህን ዘረኛ መንግሥስትና ሥርዓት በማስወገድ ለትውልዱም ሆነ ለአገሪቱ የሚበጅ ስርአተ ትምህርት በዜጎች ሙሉ ተሳትፎ ተቀርጾ በሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ አደጋ ላይ የወደቁትን የትምህርት ተቋማትንና ባለሙያዎችን ለሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ይቻላል።

ኢመማ ገና ከመነሻው ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ የወያኔ/ኢህአዴግ የትምህርት ፖሊሲ መምህራንን ፣ ተማሪዎችን ፣ ወላጆችን ፣ ሌሎች አግባብ ያላቸው ባለሙያዎችን ያላከተተ ፣ በውይይትም ያልዳበረ ሁሉም ባለድርሻዎች ( *Stake holders)* በይሁንታ ያላጸደቁት ስለሆነ "**ትውልድ ገዳይ**" ነው ብሎ አመላከቷል። ሀያ የብሶትና የመብት ጥያቄዎች ባቀረበበት ሰነድም የትምህርቱን ጉዳይ ቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ አካቷል። በሂደቱም በማህበሩ አመራሮችና በአባላቱ ላይ ዘርፋ ብዙ ጥቃት ደርሶ መስዋእትነት ተከፍሏል። የትምህርት ጉዳይ የሀገር ፣ የአጠቃላይ ሕዝብ ጉዳይ የመሆኑን ያህል ኢመማና አባላቱ ሕዝባዊ አደራ ለመጠበቅና ሙያዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ከአምባገነኑ ሥርዓት አራማጆች ጋር ግብግብ ሲገጥሙ በሚፈለገው መጠን የሕዝብ አጀብና እገዛ አላገኙም። ከሃያ ዓመታት በኋላ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል የተፈጸመውንና እየተፈጸመ ያለውን ደባ በማያወላውል መልኩ የተረዳ ስለሆነ ታቃውሞውን እየገለጸ ነው። በቅርቡ የትምህርቱን ፖሊሲና በካድሬ መምህራን የሚደረግባቸውን ደባ በመቃወም በአየር ጤና ፣ መድኃኔዓለምና ያከቲት 12 የመሰናዶ ት/ቤቶች ተማሪዎች የታየው እንቅስቃሴ በወላጆችም መታገዙ ይበል የሚያሰኝ ነው። እዚህ ላይ አንድ ሁነኛ ነጥብ ማንሳት እንፈልጋለን። የትምህርት ጉዳይ የሕዝብ ጉዳይ መሆኑ ፣ የአገር ጉዳይ መሆኑ አጠያያቂ ካለመሆኑ አንፃር ጥያቄው በማንም ይነሳ የትም ይነሳ መልስ እንዲያገኝ በጋራ መቆምና በሚፈለገው የትግል ስልት ሁሉ መሳተፍ የዜጎች ሁሉ የግዴታ ድርሻ ነው። በጋራ ጉዳያችን በጋራ መቆምና መረባረብ ካልቻልን የምንፈልገው ነፃነት ፣ የምንፈልገው ዕድገት ፣ የምንመኘው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እየራቁብን ይሄዳል። ትውልዱን ከውድቀት ለመታደግና አገርን ከጥፋት ለመጠበቅ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ከተማሪዎች፣ ከመምህራንና መብታቸውን ለማስከበር ከሚታገሉት ክፍሎች ጎን እንዲቆምና እንዲታገል በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ በድጋሚ ጥሪውን ያቀርባል።

"ትውልድ ገዳይ" የትምህርት ፖሊሲ በገዳይነት መቀጠል የለበትም !!
ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም በዕኩልነት ይዳረስ!!



P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com